የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን ነሀ. 2 ÷ 20

# ሐመረ ኖኅ

በማኅበረ ቅዱሳን በሰሜን አሜሪካ ማዕከል የሚዘጋጅ ወቅታዊ ጋዜጣ

፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ መጋቢት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

## የሰሜን አሜሪካ ማዕከል 9ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሎስ አንጀለስ ይካሄዳል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን የሰሜን አሜሪካ ማዕከል 9ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሎስ አን ጀለስ ግንቦት 18 እ 19 ይካሄዳል። ማዕከሉ እስካሁን በዴንቨር፡ በዳላስ እና በዋሺ ንግተን ዲሲ ሁለት፡ በአትላንታ እና በሚኒያፖሊስ አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ አካሂዶአል፡፡ የጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊ አባላት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢመጣም የአባላት ተሳታፊዎች ቁጥር ከ120 ከፍ ብሎ አያውቅም፤፤ የማዕከሉ ጠቅላላ ጉባኤ በሎስ አንጀለስ ሲካሄድ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ ሲሆን ፣ ከ150 በላይ አባላት በጉባኤው እንደሚገኙ ይገመታል።



ከመጋቢት 1 እስከ 15 ቀን 1999 ዓ.ም በማኅበረ ቅዱሳን የተሰጠውን የመምህራን ሥልጣ ያጠቀናቁ ከኦሮሚያ ክልል ከተለያዩ ዞኖች የተውጣጡ የሥልጠው ተመራቂዎች።

ሥልጠናው 22000.00 /ሃያ ሁለት ሺሕ/ ብር የፈጀ ሲሆን ወጪውንም የሸፈነው በሰሜን አሜሪካ የዳላስ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ካቴድራል ነው፡፡

## ሐመረ ኖኅ

የኖኅ መርከብ የጥንቲቱ
የሕያው ፍጡር ሕይወቱ
ዓለም በጥፋት ውኃ ሲነፍር
ሸሽጋ ያዳነች የሰውን ዘር
ከሐመረ ኖህ መርከቢቱ
ከምታደርሰን ከቤቱ
ከምታድነን ከጥፋቱ
ቶሎ እንሳፈር ተሳፈሩ
ወድቀን እንዳንቀር እንዳትቀሩ።

## በጅማና በኢሉባቦር ጉዳት ለደረሰባቸው ምእመናን ርዳታ ተሰጠ

http://www.eotc-mkidusan.org/Amharic/Zena

በጂማና በኢሉባቦር አህጉረ ስብከት በአክራሪ ሙስሊሞች ምክንያት በተከሠተው ችግር የተነœ ጉዳት ለደረሰባቸው ምእመናን በማኅበረ ቅዱሳን የተሰባሰበው ርዳታ ተሰጠ፡፡

በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በዴዴሳ ወረዳ ደንቢ ከተማ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊ ዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢት 8 ቀን 1999 ሽ.ም በተደረገው የመጀመሪያ ዙር ርዳታ ቤታቸው ለተቃጠለባቸውና ለፈረሰባቸው ቤታቸውን ለመሥራት እንዲ ችሉ የሚያግዝ ሁለት ሺሕ ስልœ ቆርቆሮ ቀርቦ ለሃምሳ አንድ አባ ወራዎች ለእያንዳንዳቸው አርባ ቆርቆሮ ከሚስማር ጋር የተሰጠ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ለሁለት መቶ ዘጠና አራት ሰዎች አንድ መቶ ኩንታል በቆሎ፣ ስልœ ሁለት ኩንታል ጤፍና አርባ ƒስት ኩንታል ማሽላ የምግብ እህል እና የተ ለያዩ አልባሳት እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡

በወረዳው ለሚገኙ አሥር አብያተ ክርስቲያናትና አምስት ሰንበት ት/ቤቶች አገልግሎት የሚውል ዘጠና ስድስት መጽሐ ፍ ቅዱስና ለአራት አብያተ ክርስቲያናት

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## «የኢትዮጵያ ድንኳኖች»

ትን. ዕን. ፫፥፯

ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ፣ ምስካየ ኅዙናን ፣ ሀገረ እግዚአብሔር ፣ ሀገረ ገነት ወዘተ ... ስትባል የኖረችው ያለምክንያት አይደለም። ኢት ዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያውቋት ፣ ደጋግመው የጠቀሷት ምግባር ሃይማኖቷ የተመሰከረላት ሀገር ናት።

ቅዱሳን የተመላለሱባት ፣ የቅዱሳን አጽም ያረፈባት ፣ በቅዱሳን ጸሎት ተጠብቃ የኖረች ናት ኢትዮጵያ። ነቢየ እግዚአብሔር ዕንባቆም በትንቢት መነጽር የኢትዮጵያውያንን እንግዳ ተቀባይነት ተግሮአል። /ዕንባ. ፫፥፯/ ቅዱሳን መጻሕፍት ስለ ኢት ዮጵያ ደንኳኖች የሚገሩት እንግዳ ተቀባይነትን ነው።

ዕንባቆም «የኢትዮጵያ ድን ኳኖች ሲጨነቁ አየሁ» ማለቱ አምላኳ ከቅድስተ ቅዱሳን ከን ፅሕተ ንጹሐን ቅድስት ድንግላ ማርያም በተዋህደው ሥጋ ኢት ዮጵያን መኅብኘቱን መባረኩን በትን ቢት ለመግለጽ ነው። ኢትዮጵያ እመቤታችንን እና ልጇን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በስደታቸው ወቅት ተቀብላ በማስተናገዷ ሀገረ እግዚአብሔር የተሰኘች ሀገር ነች።

ዛሬም ኢትዮጵያውያን በድንኳን የተመሰለ ቤታችን የእንግዶች መቀበያ ሊሆን ይገባዋል። ሎጥ መለአክትን ፣ አብርሐም ሥላሴን ፣ ኢትዮጵያ አምላኳን እና ወላዲተ አምላክን ያስተናገዱት በእንግዳ ተቀባይነታቸው ነው። በዚያ ዘመን የነበሩ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ጌታችንን እና እናቱን እንደተቀበሉ ፣ እኛም ዛሬ ለተራቡ በማብላት ፣ ለተጠሙ በማጠጣት ፣ ለታረዙ በማልበስ ፣ ለተቸገሩ በመርዳት ጌታችንን ልናስተናግደው ይገባል ፤ ጌታችን በወንጌል «ከእነዚህ ከታሾቹ ለአንዱ ያደረጋችሁትን ለእኔ አደረጋችሁት» በማለት ተግሮአል። /ማቴ ፳፭፥፵/

ለቃለ እግዚአብሔር፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ዜና ለማግኘት፡ ስለ ማኅበሩ አገልግሎት ለመረዳት እና ለማወቅ፡ የበዓላት እና የአ ጽዋማት ጊዜን ለማወቅ የማኅበሩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡ www.eotc-mkidusan.org

# እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ

## የማዕከሉ መልእክት

«ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና» ሮሜ 13፡11

ብርሃነ ዓለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ምእመናን በጻፈላቸው ክታቡ ከስንፍና፣ ከቸልተኝነት፣ ከኃጢአት . . . ወዘተ እንቅልፍ ተላቅቀው ለጽድቅ እንዲነሳሱና ለወንጌል አገልግሎት እንዲነቃቁ መክሯቸዋል፡፡ ለዚህም የጨለማ ሥራን /ኃጢአትን/ ከሕይወታቸው እንዲያስወግዱ ነግሯ ቸዋል፡፡ እኛም የዚህ ዓለም ወጥመድ እንዳያሰጥመን አምላካችን የሰጠንን ተስፋ እየጠበቅን በንቃት መነሳትና ለተšለ አገልግሎት መዘጋጀት ይኖርብናል፡፡

እኛም ቤተክርስቲያናችንን በእውቀታችን፣ በጉልበታችንና በገንዘባችን ለማገልገል ወደንና ፈቅደን የተሰበሰብን የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ያለፈውን አገልግሎታችንን ገምግመን፣ በአንጻሩ ቤተ ክርስቲያናችን ከእኛ ምን ያህል እንደምትጠብቅ ተገንዝበን ለተšለ አገልግሎት ልንነሳ ይገባል፡፡ በአለፈው ዓመት በሚኒያፖሊስ፡ ሚኔሶታ በተደረገው የንዑስ ማዕከላችን 8ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የወሰናቸው ውሳኔዎች ምን ያህል ተግባራዊ ሆነዋል? ለማኅበራ ችን ዓላማ ስኬት ምን ያህል አስተዋጽኦ አበርክተናል? የሚሉትን ጥያቄዎች በሚገባ መመለስ ይጠበቅብናል፡፡ ዛሬ መሥራት ያለብንን ካልሠራን ለመጪው ትውልድ የምናቆየው የተበላሸ ታሪክ እንዳይሆን ያሰጋልና፡፡ ከእንቅልፋችን ልንነቃ ይገባናል፡፡

የትንሣኤውን ብርሃን ያዩ ሐዋርያት ለበለጠ አገልግሎት ተነቃቅተዋል፡፡ እኛም በተለያዩ ምክንያት ከሀገር ከወገን ርቀን ከአምልኮተ እግዚ አብሔር ይልቅ የሥጋ ፈቃድ ብቻ በሚፈፀምበት በባዕድ ሀገር የምንገኝ ምንም እንኳን በምግባር ብንደክም ትንœኤውን እያሰብን እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ከተዘናጋንበት የጥድፊያ ዓለም ልንወጣ እና በአገልግሎት ልንኖር ይገባናል፡፡ ለሥጋችንን ተድላ ብቻ በማሰብ እና በመጨነቅ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እና አገልግሎታችን ጊዜ አጥተን ከባድ ወጥመድ ውስጥ እንዳንወድቅ ጊ ዜያችንን በዕቅድ መጠቀም፣ ሌሎች ወንድሞችና እህቶችም ጊዜያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ በመመልከት የቅዱሳን በዓት ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሳለመራቅ በጸሎት ጭምር ድርšችንን ልንወጣ ይገባናል፡፡

በቀረውስ የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

**በማኅበረ ቅዱሳን በሥርጭት ላይ የዋሉ የትምህርት ዝግጅቶች**

**መጻሕፍት**

1. **ምስጢሬን ላካፍላችሁ - ቁ. 3**
2. **በዓላት**
3. **የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች**

**ሲዲ**

1. **በተለያየ ርእስ 10 ትምህርቶች በሲዲ - በቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው**
2. **«በባቢሎን ወንዞች መካከል»** በሚል ርዕስ ትምህርታዊ ልብ ወለድ ትረካ *(ድርሰት በዲ/ን ኤፍሬም እሸቴ)*
3. **የጠፋው ጌጥ -** *በዲ/ን ብርሃኑ አድማሴ*
4. **ሌሎች ተምህርቶች እና መዝሙሮች**

**ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ትምህርቶች እና ሌሎችንም ፣ እንዲሁም ሐመር እና ስምዐ ጽድቅን ለማዘዝ ከዚህ በታች በሚገኙት የስልክ ቁጥሮች ወይም የኢ-ሜይል አድራሻ መጠየቅ ትችላላችሁ፦**

**ስልክ፡** 202-486-1513 **ወይም** 214-718-8713

**ኢ-ሜይል፡** **eotcmkusa_development@yahoo.com**

# የቅዱሳን አማላጅነት

*ቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን*

**ቅዱስ**፡ – የቃሉ ትርጉም ልዩ፡ – ምስጉን፡ – ክቡር ማለት ነው። ሰው ወይም ማንኛውም ነገር ለእግዚ አብሔር አገልግሎት ሲለይ ቅዱስ ይባላል። ቅዱሳን መላእክት *ራዕ.5 ÷ 11*፣ ሰዎች *ዘፀ.28 ÷ 41*፣ እንስሳት *ዘፀ.13 ÷ 2* ቀኖች *ዘፍ.2 ÷ 3* ቅዱሳት መካናት *ዘፀ.3 ÷ 5።* ማንኛውም ነገር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ከዋለ ቅዱስ ሊባል ይችላል። *ኢያሱ 6 ÷ 19* እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ ለእግዚ አብሔር የሆነ ሁሉ ቅዱስ መሆን አለበት። «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ» እንዲል። *ዘሌ.19 ÷ 2*

ቅዱስ የሚለው ቃል በብዙ ቁጥር ሲነገር ቅዱሳን ይሆናል። ቅድስና የባህርይና የጸጋ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል። ቅድስና የባህርይ ገንዘብነቱ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህም ማለት ቅድስናው ከእርሱ የማይለይ፡ ከማንም ያልተዋሰው ወይንም ያልተቀበለው፡ ማንም ሊወስድበት የማይችል የራሱ ገንዘብ የሆነ ማለት ነው። እግዚአብሔር በባህርይው ቅዱስ ስለሆነ ቅድስና ከእርሱ እርሱም ከቅድስና ተለይተው የማይታሰቡ ናቸው። እግዚአብሔር በቅድስናው ርኩሰት፣ በጻድቅነቱ ሐሰት፣ በብልጽግናው ንዴት የሌለበት በመሆኑ ቅዱስ እግዚ አብሔር ይባላል። ይህንንም ቅድስናውን ሱራፌል «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች» በማለት በምሥጋና የባሕርይ ቅድስናውን ገልጸዋል። *ኢሳ.6÷3። ራዕ.4÷8*

የጸጋ ቅድስና የተሰጣቸው ቅዱሳን መላእክት እና እግዚአብሔር ከመረጣቸው ውስጥ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ቅዱሳን ነቢያት፡ ቅዱሳን ሐዋርያት፡ ሰማዕታት፡ ጻድቃን፡ ካህናት፡ ሊቃውንት ናቸው። የጸጋ ቅድስና ማለት ከእግዚ አብሔር በጸጋ /በስጦታ/ የተሰጠ ወይም የተገኘ ማለት ነው። እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ የእርሱን ፈለግ ተከትለው በቅድስና ሕይወት የተጓዙ ቅዱሳን ይባላሉ። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ «እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅ የሚያደርግ ጻድቅ ነው» ብሏል። 1ኛ ዮሐ.3÷7።

**<u>አማላጅነት፡</u>– አማላጅነት ማለት ደግሞ እግዚአብሔር ስለቅዱሳኑ ሲል ይቅር ይለናል በሚል የትህትና እና የፍቅር መግልጫ እኛ ቅዱሳኑን የምንጠይቅበት፡ ቅዱሳኑም ስለኛ የሚለምኑበት የጸጋ ሥጦታ ነው። «የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና» መዝ.33÷15 እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ማለደ ማለት የሚከተሉት ትርጓሜ ይኖሩታል። ማለደ፡–**

ሀ. <u>በጠዋት ተነሣ፡</u>– «ማልደው ተነሥተው በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ *1ኛ ሳሙ.1÷19* «አቤሜሌክም በነጋታው ማለደ ባሪያዎቹን ሁሉ ጠራ» እንዲል። *ዘፍ.20÷8*

ለ. <u>ጸለየ፡</u>– ጠየቀ፡– ጮኸ ማለት ነው። በግዕዙ ቋንቋ «ተንበለ» አማለደ ይባላል። አማለደ ማለት አንዱ ስለሌላው ለመነ፡ ጸለየ ማለት ነው። በአማላጅነት ተግባር ውስጥ ሦስት ወገን መኖር አለባቸው። እነርሱም አማላጅ፡ ተማላጅ፡ የሚማለድለት አካል ናቸው።

2ኛ. <u>አማላጅ፡</u>– ማማለድ ለፍጡር ባህርይ የሚስማማ የትህትና ሥራ በመሆኑ አማላጅ የምንላቸው ከላይ የጠቀስናቸው እግዚአብሔር የመረጣቸው ናቸው። «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው። ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው» *ሮሜ.8÷30* ይላል። ቅዱሳን አያማልዱም ማለት የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ መቃወም ነው። «እግዚአብሔር የመጠ ረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?» *ሮሜ.3÷33* የእነርሱ ተግባር በኃጥአን ፈንታ ስለኃጥአን

***(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)***

(***ከገጽ 1 የዞረ***)

የውስጥ መጋረጃ ተሰጥቷል። እንዲሁም ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ማሠሪያ የሚሆን አንድ መቶ ሃምሳ ቆርቆሮ ተዘ ጋጅቶ ቀርቧል።

ዲ/ን ግርማ መታፈሪያ፡ የማኅበኹ ዋና ጸሐፊ እርዳታው በተሰጠበት ወቅት ባደረጉት ንግግር በዴዴሳ ወረዳና በአካባበቀ.ው የተቃጠሉና የፈረሱ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ሙሉ ወጪያቸውን በመሸፈን በብሎኬት እንዲሠሩ በአፋጣኝ ሥራቸው ተጀምሮ ለማስፈ ጸም እንዲቻል ዝግጅቱ መጠናቀቁንም አስታውቀዋል።

ዐቢይ ኮሚቴው ርዳታ ለማሰባሰብ ባከናወነው ተግባር ለመጀመሪያ ዙር የአስቸኳይ ርዳታና ማቋቋሚያ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ፤ በተከሰተው ችግር የተነœ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች አስቸኳይ የም ግብ ርዳታ፣ ለተቃጠ ሉና ለፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት መሥሪያ፣ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማጠናከሪያ የሚውል በጅማ ሀገረ ስብከት ለሚገኙ አንድ መቶ አሥራ ስምንት ሺህ አርባ ብር፤ በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ለሚገኙ ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺሕ ብር፤ በምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ለሚገኙ ዘጠና አንድ ሺሕ አምስት መቶ ብር መመደቡን ገልጸዋል በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ዴዴሳ ወረዳ በደንቢ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተካኼ ደው የርዳታ አሰጣጥ መርሐ ግብረ የዚሁ አካል የመጀመር ዙር መሆ ኑንም አስታውቀዋል።

ከዐቢይ ኮሚቴው መግለጫ ለመረዳት እንደተቻለው፤ በጅማ ሀገረ ስብከት ጉዳት ለደረሰባቸው ምእመናን ርዳታ፣ ለተቃጠሉና ለፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት ማሠሪያና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማጠናከሪያ ከተመደበው አንድ መቶ አሥራ ስምንት ሺሕ አርባ ብር ውስጥ ስልœ ስምንት ሺሕ አርባ ብር በታሰበው መሠረት ለየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቱና ምእመናኑ ተሰ ጥቷል። በጅማ ሀገረ ስብከት ለጨጌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ገቢ ማስገኛ የእህል ወፍጮ ለመትከል በተያዘው ዕቅድ መሠረት ሃምሳ ሺሕ ብር ወጪ ሆኖ ግዢው እየተፈጸመ ነው።

*(ከገጽ 3 የዞረ)*

ወደ እግዚአብሔር ምልጃ ማቅረብ ነው።

2ኛ. <u>ተማላጅ፡</u>– ማለት የአማላጅ ጸሎት ወይም ልመና ተቀባይ ወይም የጸሎት መድረሻ ነው። የጸሎት ሁሉ መድረሻ ደግሞ እግዚአብሔር ነው።

3ኛ. <u>የሚማለድለት፡</u>– አማላጆች ወደ እግዚአብሔር ምልጃ የሚያቀርቡ ስለኃጥአን መዳን ነው። የሚጸለይለት ወይም የሚማለድለት ሰው በአማላጅነት ሥራ ውስጥ ድርሻ አለው። ይኸውም በአማላጅ ጸሎት እና በተማላጅ ቸርነት ማመንና ከሚሠራው ኃጢአት መመለስ ነው።

ቅዱሳን ለኃጥአን ወገኖቻቸው የሚለምኑት ልመና በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅና ተሰሚ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ምንም እንኳ ኃጥአንን በክፉ ሥራቸው ቢያዝንባቸውም በቸርነቱ የሚምርበት ምክንያት ይፈልጋልና የቅዱሳንን ምልጃ ለዚሁ ቸርነቱ መንገድ ያደርገዋል። ነገር ግን የሚማለድለት ሰው በቅዱሳን ምልጃ ተጠቃሚ ለመሆን የሚከተሉትን ሊያሟላ ያስፈልገዋል።

1. በሃይማኖቱ ጥርጥር የሌለበት አማኒ ሊሆን ይገባል። ሃይማኖት ለሌለው ሰው የሚቀርብ ምልጃ ተቀባይነት የለውም። ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፡ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉ ሕይወትን ይሰጥለታል።» በማለት ለሌላው ሰው ድኅነት እግዚአብሔርን በጸሎት መለመን እንደሚገባና በዚህም ጸሎት ለኃጥኡ ሰው ሕይወትን እንደሚሰጥ ተናገረ። በምልጃ ለሚገኘው ለእግዚአብሔር ቸርነት ብቁ የማያደርግ ኃጢአት ላደረጉ ግን መለመን እንደማይገባ «ለሞት የሚያበቃ በደል አለና ስለዚህ እንዲለምን አልልም» *1ኛ ዮሐ.5 ÷ 16*

   አለማመንና ካመኑ በኋላ መካድ ሥርየት የሌለው ኃጢአት ነውና። «ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚ አብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለምን ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው።» *ዕብ.6 ÷ 5* ስለዚህ የምልጃ ጸሎት የሚደረገው ሃይማኖት እያላቸው በምግባር ለደከሙና ለተሰነካከሉ ሰዎች ነው። ሃይማኖቱን ለካደ፡ ለተጠራጠረ /መናፍቅ/፡ ለኢጥሙቅ /ላልተጠመቀ/ ምልጃ አይደረግም። *ማቴ.12 ÷ 32 – 32 2ኛ ጴጥ.2 ÷ 20 – 22*

2. በቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ በመታመን የእግዚ አብሔርን ምህረትና ቸርነት የሚፈልግና የሚናፍቅ ሊሆን ይገባል።

3. እርሱም የሚችለውን ያህል ልቡን ወደ ፈጣሪው መልሶ የእግዚአብሔርን ገጸ ምህረት ደጅ ሊጠና ያስፈልጋል። አብርሃምን ሲለምን የነበረው ባለጸጋ ያልተጠቀመው በዚህ ዓለም ሳለ የሠራው ሥራ በረድኤተ ቅዱሳንና በእግዚአብሔር ቸርነት ለመጠቀም የማያበቃው ስለነበረ ነው።

ቅድስት ቤተክርስቲያን በቅዱሳን አማላጅነት ስለምታምን የዘላለም መታሰቢያ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን በስማቸው አንፃ፡ ጽላት ቀርፃ፡ ድርሳን፡ ገድል፡ መልክ ጽፉ ደጉሳ በጸሎታቸው ትማፀናቸዋለች። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና። «ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔን ስለሚይዙ፡ በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶት ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ። የማይጠ ፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ።» ይላልና። *ኢሳ. 56 ÷ 4 – 5* መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በማይታበለው መለኮታዊ ቃሉ «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፡ – እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፡ – ጻድቁንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠ ፋብትም» *ማቴ.10 ÷ 40 – 42* ስላለ የቅዱሳን ወዳጆች የሆኑ በአማላጅነታቸው የሚያምኑ ሁሉ ወርኃዊም ይሁን ዓመታዊ ክብረ በዓላቸውን እየጠ በቁ ይዘክራሉ ነዳያንን ይመገባሉ። *ሉቃ.14 ÷ 12 – 14* በዚህ ሁሉ የሚመሰገነው የፍጥረታት ባለቤት እግዚ አብሔር ነው።

**ሀ. <u>ምልጃ የእግዚአብሔር ትዕዛዝና ፍቃድ ነው።</u>**

ምልጃ በሰው ፈቃድ የተደረገና የተጀመረ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲፈጽሙት ያዘዘውና የፈቀደው ነገር ነው። አብርሃም ወደ ጌራ ራ ተሰዶ ሳለ የሀገሩ ንጉሥ አቤሜሌክ ሚስቱን ሣራ ን ሊቀማው ባለ ጊዜ እግዚአብሔር ሌሊት በሕልም ሣራን እንዲመልስለት ካዘዘው በኋላ «ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል፡ ትድናለህም» በማለት እግዚ አብሔር አቤሜሌክን፡ አንተ ወደ እኔ በቀጥታ ጸልይ፡ ሚስቱን ግን መልስ ማለት ሲችል ነቢይ ነውና ስለአንተ ይጸልያል ለምን አለው ? አቤሜሌክን አብርሃም እንዲጸልይለት ራሱ

***(ወደ ገጽ 5 ዞሯል)***

በሰሜን አሜሪካ ማዕከል
ፍኖተ ሰላም ሬድዮ

**Denver, CO**
**Atlanta, GA**
**Washington, DC**
**www.radiotewahedo.org**

*(ከገጽ 4 የዞረ)*

እግዚአብሔር ነገረው:: *ዘፍ.20 ÷ 1 – 7* ራሳችን በቀጥታ እንጸልያለን፤ አማላጅ መፈለግ መንገድ ማብዛት ነው የሚሉ ሰዎች አካሄዳቸው ልብ ወለድና የድፍረት አካሄድ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ልብ ማለት ይገባል:: እግዚአብሔርን የምናገኘው እራሱ ባሳየን መንገድ እንጂ እኛን በመሰለን መንገድ አይደለም:: ጠቢቡ ሰሎሞን «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍፃሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው» ያለው እንደዚህ ያሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚያስቡ ሰዎች የሚሄዱበትን መንገድ ነው:: *ምሳ.14 ÷ 12*

ኢዮብን ሊጠይቁት የመጡትን ሦስቱን ጓደኞቹን «እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል::...ባሪያዬ ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፡ እኔም እንደስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ» አላቸው:: ራሱ እግዚአብሔር በረድኤት ተገልጦ እያነጋገራቸው እያለ በቀጥታ ወደ እኔ ጸልዩ፡ ይቅር እላችኋለሁ አላለም:: ተፈትኖ የወጣውና እንደ ወርቅ የነጠረው ወዳጁ ኢዮብ ክብሩ ይገለጽ ዘንድ ስለ እነርሱ እንዲጸልይላቸው ወደ እርሱ እንዲሄዱ አዘዛቸው እንጂ:: በዚሁ መሠረት እንደታዘዙት ሲያደርጉ ኢዮብ ስለ እነርሱ ጸለየ፡ «እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት ተቀበለ» የኢዮብ ፊት ማለቱ ኢዮብ ስለ ሦስቱ ጓደኞቹ ያቀረበውን ምልጃ ነው:: *ኢዮብ 42 ÷ 7 – 9*

ቅዱስ ጳውሎስ አማላጅነት የቅዱሳን ሥራ መሆኑን ሲገልጽ «በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ:: እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን» ብሏል:: *2ኛ ቆሮ.5 ÷ 20* እግዚአብሔር ወዳጆቹ ቅዱሳን ስለደካሞች እንዲለምኑት በእነርሱ የማማለድ ጸጋና ቃል አኖረ:: እንዲሁም «በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚ አብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ» ይላል:: *ፊል.4 ÷ 6*

ስለዚህ ምልጃ ራሱ እግዚአብሔር ያሳየው መንገድ ነው:: አማላጅነት የእግዚአብሔር የቸርነቱ ጸጋ /ስጦታ/ ነው:: ምክንያቱም ምግባራቸው የደከመና ጸሎታቸው እንደ እርሱ ፈቃድ ያልሆነ ተነሳሕያን ኃጥአን የእርሱን ፈቃድ በሚያውቁና በሚፈጽሙ በምግባር በትሩፋት በበለጸጉ ጻድቃን እንዲረዱ ማድረጉ የቸርነቱ መግለጫ ነው:: ስለዚህ ምልጃ የእግዚ አብሔርን ፈታሒነትና /ፈራጅነት/ የሚጋፋ ሳይሆን ቸርነቱን የሚገልጽ ነው:: ከአባታዊ ደግነቱ የተነሳ ሁሉም እንደ ወዳጆቹ እንደ ጻድቃን ካልሆኑ ሳይል በጻድቃን ጸሎት ኃጥአን እንዲጠቀሙ አደረገ:: ይህን ግን ራሱ እግዚአብሔር የወደደውንና የፈቀደውን የአማላጅነት ነገር የሚቃወም ቢኖር ክርክሩ ከባለቤቱ ከእግዚአበሔር ጋር እንጂ ከሰው ጋር አለመሆኑን መገንዘብ ይገባል::

**ለ. <u>የቅዱሳን አማላጅነት በሕይወተ ሥጋ፡ –</u>**

*... ይቀጥላል::*

## የምድር ጨው ችሁ።

እግርህን ወደ ጽድቅ ወደ ቤቱ መርቶ
ና ብሎ ጠርቶሃል ሥጋ ለሰብሶ መጥቶ
ንቁ ሐዋርያ እንድትሆነው ሽቶ
ተምረህ ከቃሉ ድኅነትን ለማብሠር
የወደፊት ተስፋ እንድታገኝ ክብር
ምድርን አለምልማት በቃለ እግዚአብሔር
ድምጽህን ስትሻ እናት ተዋሕዶ
ርቀህ አትሸሻት ኑሮህ ቢታይ ከብዶ
ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል
ውጪ ተወርውሮ በእግር ይረገጣል
ና ይልቅ ወዳጄ ወገብህን ታጥቀህ
ችለህ መከራውን መስቀሉን አንግበህ
ሁናት መከታው ሁሉን አሳልፈህ።

## ምክረ አበው

- *«ጢስ ንቦችን ከቀፎ እንደሚያባርራቸው ከተግባራቸውም ውስጥ ጣፋጭነትን እንደሚያስወግድባቸው ሁሉ ሥጋዊ ቅንጦትም ከነፍስ ውስጥ ፈሪሃ እግዜአብሔርን ያስወጣል፡ ተግባርዋንም ሁሉ ያበክንባታል»*
- *«የወንድማችንን ጥፋት በሠወርን ጊዜ እግዚ አብሐርም የኛን ይሠውርልናል፤ የወንድማችንን ጥፋት በገለጥን ጊዜ ደግሞ የኛን ይገልጥብናል::»*
- *«ፈሪሃ እግዚአብሔር ካደረበት ሰው ጋር አብረህ ኑር፤ እርሱ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ያስተምርሃልና::»*
- *«ከመጠን ያለፈ ነገር ሁሉ የሚመጣው ከአጋንንት ነው::»*
-

*አባ ጴሜን ዘገዳመ አስቅጥስ*
ምንጭ:- በበረሐ ጉያ ውስጥ
1998 ዓ.ም.